የኖሩበት ዘመን

• አንደኛ : የወቅቱ ፖለቲካዊው ሁኔታ

ሸይኹል ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ የኖሩበትን ዘመን የሚመረምር የጥናት ባለሙያ በወቅቱ የነበረውን ተጨባጭ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በሶስት ዋናዋና ነጥቦች ከፍሎ መግለጽ ይችላል :

ሀ) ተታሮች የእስልምናውን ዓለም የወረሩበት ወቅት ፤

ለ) ፈረንጆች የእስልምና ዓለም በጦር ያጠቁበት የሰቆቃ ወቅት እንደሆነና

መ) የእርስ በእርስ ጦርነት ያየለበት በተለይም በነገሥታት(ማማሊኮች) ፣ በተታሮችና በሙስሊሞች መካከል የነበሩ የእርስ በእርስ ጦርነቶች የተስተናገዱበት ወቅት እንደነበር መግለጽ ይቻላል ።

ኢብኑል አሲር ረሒመሁሏሁ ተዓላ[24] በዚያው ዘመን የኖሩ ሊቅ ናቸው ። ስለነዚያ ወቅታዊ ክስተቶች ንጥጥር ባለመልኩ ገልጸው አስረድተዋል ። ((*እስልምና እና ሙስሊሞች በዚህ ዘመን የትኛውም ትውልድ ያላስተናገደውን ሰቆቃና መቅሰፍት በመሸከም ለስቃይ ተዳርገዋል ። እለታቂ ድርጊቶችን ሙስሊሞች ላይ ከፈጸሙት ጎራዎች ውስጥ እንዱ ተታሮች ናቸው ። ከነርሱም መካከል ከምስራቅ በመምጣት ዘግናኝ ድርጊታቸውን የሰማ በሙሉ ውስጡን የሚያሸብር እስከፊ እረመኔያዊ ድርጊት ፈጽመዋል ። ሌሎች የዚሁ የእለታቂ ጭፍጨፋ አራማጆች - የእሏህ እርግማን በነርሱ ላይ ይውረድና- ፈረንጆች ናቸው ። እነዚህ እረመኔዎች ከምዕራብ በመጀመር ወደ ሻም ምድር ዘልቀው በመግባት ግብጽን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ዓላማ እድርገው በመነሳት ሙስሊሞችን በሚዘገንን የጭቃኔ ድርጊት ሰቆቃ እድርሰውባቸዋል ። የእሏህ ቸርነቱ ሙስሊሞችን ታድጓቸው በፈረንጆች ላይ ድል ባይቀናቸው ኖሮ ደምያጥ የተሰኘችውን የድንበር ላይ ወሳኝ ምሽግ እና መላውን የግብጽ መንደሮች ለመቆጣጠር በቻሉ ነበር ። ሌላው ሙስሊሞች እራሳቸው እርስ በእርሳቸው ሰይፍ በመማዘዝ እንዱ ሌላውን ለማጥፋት የዘመቱበት የፈተና ወቅት ነበር ።*)) [25]

ተታሮች በሂጅራ አቆጣጠር በሰባተኛው ምዕተ-ዓመት በሙስሊሞች ላይ የተደነቡ መቅሰፍቶች ነበሩ ። እነርሱ ሙስሊሞች ላይ በመዝመታቸው በግዳድ ከሙስሊሞች እጅ ልትወጣ ቻለች ። ተታሮች ሙስሊሞችን ማጥቃታና መጭፈጨፍ የጀመሩት ባግዳድ ከሙስሊሞች እጅ ሳትወጣ በፊት በዓመታት ቀደም ብሎ ነበር ። ኢብኑ አሲር ረሒመሁሏሁ ተዓላ (በ630 ዓሂ ነው ሕልፈታቸው) የ617 ዓ.ሂ. ከስተት ለማውራት እየሰቀቃቸው ለዓመታት ሳያወሩት ፤ ለሚጠይቃቸው ሰው ፊታቸውት በማዞር ጥለውት እየሄዱ ትዝታውን ለመርሳት ሲሞከሩ ቆይተዋል ። *((ኧረ ለመሆኑ ኣንዮቱ ሜኾከኖ ኣሰልምና ላይ የተረባረቡትን ከብረ -ነክ ድርጊቶች ኣና ሙስሊሞች ላይ የደረሰውን ኣረመኔያዊውን የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ታሪክ መጻፍ የሚችል ኣጅ ያለው ኣንድሰ ይኖራልን ?! ኧረ ኣንዲያው ማን ይሆን ይህን የሰው ኣውሬዎች የፈጸሙትን የሜኾካኔ ድርጊት ለመጻፍ ኣጁ የሚታዘዝለት? ማን ሊናር ይችላል? ያንንሰ ሰቆቃ ከማየት ዋ ምነው ኣናቴ ባልወለደችኝ ?! ምን ነበር ከዚያ ከስተት በፊት ሞቼ ወይም ተረስቼ ብቀር ?!))* [26] ሲሉ ነበር የገለጹት ። በዚህም ሽንፈት-ባግዳድ ከሙስሊሞች እጅ እንድትነጠቅ ባደረገው የሽንፈት ጦርነት- ምክኒያት የዐባሳውያን ሥርወ-መንግሥት ሊወድቅ ቻለ (656 ዓ.ሂ)። ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ኢብኑ ተይሚየህ ተወለዱ *((ተታሮች ያደረሱትን ውድመት የሚያሳዩ ፍርሰራሾችን በዓይናቸው ሳያዩ ኣልቀሩም ፤ የከስተቱን ዝርዝር ጉዳይ በወቅቱ የነበሩት የዓይን ኣማኞች ኣና ከስተቱን ያስተናገዱት የሰቆቃው ሰለባዎች ገልጸውላቸዋል ። ይህን ታሪክ ሲሰሙ ያ ውሰጣቸውን የሞላው ለዲናቸው የመቆርቆር ጥልቅ ሰሜት ኣንደሚግልና በነዚህ ኣረመናዊው ተግባር ላይ በተሰማሩት ጭራቆች ድርጊት ውሰጣቸው ኣንደሚበግን ኣያጠራጥርም ።))* [27]

ፈረንጆች ወይም የመስቀል ጠረኞች ያደረጉትን ወረራ ሙስሊሞች ከፍተኛ ኣልቂትን ካስተናገዱ በኋላ ኃይላቸውን ኣጠናከረው ከርስቲያን መስቀለኞችን እያሳደዱ ማደካም በጀመሩበት ኣራተኛው ዙር ፍልሚያ ላይ ነበር ኢብኑ ተይሚየህ

ረሒመሁሏሁ የተወለዱት ። በወቅቱ ሙስሊሞች በክርስቲያን መስቀለኞች የተነጠቁትን አገሮቻቸውን ማስመለስ የጀመሩበት ወቅት ነበር ።

የእርስ በእርስ ጦርነቱ ፈተና የተከሰተው ሌሎች ሙስሊሞች እና ሙስሊም የሆኑ ተታሮች መካከል የተፈጠረው የነገሥታት (የመማሊኮች) እርስ በእርስ መናቆር ያስነሳው ጦርነት ነው ። ይህም የእርስ በእርስ ጦርነት *የመማሊክ ሹማምንት ጦርነት* በመባል ይታወቃል ። በዚህ የእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት ሸይኹል ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ የመጨረሻውን የመማሊክ አሚር የሙስሊሞች ደም በከንቱ እንዳይፈስ ፣ ዝርያዎቻቸውም ጠፍተው እንዳይቀሩና ክብራቸው ተገፍፎ ተዋርደው በታሪክ መዝገብ ውስጥ ጥቁር አሻራ ጥለው እንዳያልፉ በመገሰጽ የተወሰኑ መግባቶችንና እርቅ እንዲፈጠር በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ። ይህም ታሪካዊ ከስተት የታሪክ ጸሐፍቶች ጽፈው ያኖሩት ታሪካዊ ገድላቸው ነው ። [28]

- ሁለተኛ : በወቅቱ የነበረው ማህበራዊ ሁኔታ

በወቅቱ ሙስሊሞች አገራቸው ውስጥ በነበረው የፖለቲካ ነውጥና አለመረጋጋት ምክኒያት የሙስሊሙ ማህበረሰብ ከተለያዩ ዝርያዎች የተዋሐዱ የዘር ስብጥሮች ነበሩ ። ተታሮቹ ከምስራቁ ዓለም እምነታቸውን ፣ ባህላቸውን ፣ ፈሊጦቻቸውን ፣ ብሂሎቻቸውን ፣ ተፈጥሯዊ ባህሪያቸውን ፣ ሥነ-ምግባራቸውን ይዘው የመጡበት ወቅት ነው ። በሌላም ረገድ ከመስቀላውያኑ በወቅቱ በሙስሊሞች እጅ የገቡ የፈረንጅ ምርኮኞች ፣ ቱርኮች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ማህበረሰቡ በሚተዳደርበት ማህበራዊ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ መፍጠር ችለዋል ። ሁሉም በዚህ እስላማዊ ማህበረሰብ ውስጥ ሲኖር የየራሱ ባህል ፣ ቋንቋ ፣ ልምድ እና አመለካከት ያለው በመሆኑ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ በባህሉ ፣ በቋንቋው ፣ በልምዱ እና በአመለካከቱ ላይ ከፍተት ፈጥሯል ።

በተጨማሪም በየኢስላማዊ "አውርጃዎች" ይኖሩ የነበሩት ሙስሊሞች በተታሮች እና በሌሎችም ጠላቶች በተቆሰቆሰው ሙስሊሞችን ከምድረ- ገጽ ለማጥፋት የታለመ ጦርነት ምክኒያት ወደ አጎራባ ች"አውርጃዎች" ይሸሹ ነበር ። ዒራቅ "አውራጃ" ውስጥ የነበሩት ሙስሊሞች ወደ ሻም ይሰደዱ ነበር ። የዲመሽቅ ነዋሪዎች ወደ ግብፅ እና ሞሮኮ ፤ ሌሎችም ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች ይሸሹ ነበር ።

እነዚህ መንስኤዎች ተደማምረው የሙስሊሙ ማህበረሰብ ወጥ ሥርዓት የሌለው የማህበራዊ መዋቅር እንዲኖረውና ማህበረሰቡ ከተለያዩ የማህበረሰብ አካላት ጋር ተሰባጥሮ ኢስላማዊ ይዘቱን በማጣት ከሌሎች ባህሎች ፣ ልማዶች እና የእምነት አመለካከቶች ሊቀየጥ ችሏል ። ይህ አደገኛ ማህበራዊ ቀውስ እስልምና የማያጸድቃቸውን ባዕድ ተግባራት ፣ የማይቀበላቸውን የተዛቡ የእምነት አመለካከቶችን ፣ ሸሪዓን የሚጻረሩ ሰርጎ ገብ ጽንሰ አሳቦች እና ጸረ ኢስላም ባህሎች እየተሰገሰጉ የእስልምናን ልብስ ተላብሰው ሰርገው በመግባት እምነቱ እንዲበበረዝ አደረጉ ። በዚህ አደገኛ የትርምስ ወቅት እኒህን ታላቅ ኢማም አሏህ ተባረከ ወተዓላ ለዚህ እምነት ጠበቃ አድርጎ በመላክ ሰርጎ ገብ አመለካከቶችን ፣ ተግባራትን እና ጸረ ኢስላም አቋሞችን መንጥረው ለማስወገድ ቻሉ ። [29]

• ሶስተኛ : በወቅቱ የነበረው የዕውቀት ሁኔታ

በሸይኹል ኢስላም አሕመድ ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ዘመን የዕውቀት ውጤቶች በሙሉ የተመናመኑበት እና ከስሞ የጠፋበት ወቅት ነበር ። አእምሮዎች ከዕውቀት አድማስ ርቀው የማሰላሰያ መሣሪያቸው የሆነውን ብሩሕ ጭንቅላት ቆልፈው በጭፍን ተከታይነት ግትር አቋምን ፣ ጎጠኝነትን ጽንፈኝነትን እና ወገንተኝነትን መርጠው የሚራመዱበት የጽልመት ወቅት ነበር ። በወቅቱ የነበሩ የዕውቀት ባለቤቶች ይሰሩት የነበረው ከፍተኛው ሥራ የቀደምት ሊቃውንት ንግግሮችን አንድ ላይ በማጣመር ያለምንም ድካም የድምራቸው ውጤት ምን እንደሆነ ብቻ ለመግገንዘብ የሚደረግ ሙከራ እንጂ ሌላ አዲስ የዕውቀት ፍሬ ለማበርከት

የሚደረጉ ጥናቶችን በወቅቱ እየሠሩ አልነበሩም። ይልቅ ረጃጅም መጽሐፍት መጻፍ እና ረጃጅም የነበሩትን መጽሐፍት አጠር አጠር አድርጎ በማቅረብ ሥራ ላይ ተጠምደው ነበር ። ምንም ዓይነት አዲስ የዑለሞች ግኝት ወጥቶ ለሕዝብ ሲቀርብ አይስተዋልም ። የስንፈትን ኩታ የተላበሱ ትውልዶች የተበራከቱበት ዘመኖች በሙሉ ልዩ መለያቸው በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አያሌ ንግግሮችን በመሰብሰብ እና ስለአንድ ርዕስ የሚያወሩ መጽሐፍትን በመቆለል አንድ አዲስ አሳብና ገንቢ የሆነ ግኝት ከፊታቸው ከቆለሏቸው መጽሐፍት ውስጥ ማውጣት ሳይችሉ ያለፉት ይደጋግሙት እንደነበረው እነርሱም ያንኑ በመደጋገም ጊዜን በከንቱ በመግደል ማለፍ የሚለዩበትልዩ ምልከታቸው ነው ።

አንዳንድ የጥናት ባለሙያዎች በዚህ ዘመን የተስተዋለውን መሳነፍ እና አዲስ የአእምሮ ውጤት ሙስሊሞች ከዑለሞቻቸው ያላገኙበትን ምክኒያት ሲተነትኑ" በወቅቱ የነበሩት የሙስሊም ነገሥታት ፣ ቱርኮች እና መማሊኮች በመሆናቸው የመግባቢያ የቋንቋቸው ዐጀም ስለሆነባቸው አእምሮ ከአእምሮ ጋር መናበብና መግባባት ስላልቻለ ፤ የተለያዩ ቋንቋዎች የፈጠሩት ከፍተት አሳባቸውን ለመለዋወጥ ስላቀባቸው እና የተለያዩ አደጋዎች ሙስሊሞች ላይ ከየአግጣጫው በመትመም ስላጣደፋቸው በተረጋጋ መንፈስ ሰከነው በመቀመጥ አእምሯቸውን ለማሰላሰያነት መጠቀም ችለው አዲስ የዕውቀት ግኝት ላይ በመድረስ ለማህረሰቡ አዲስ ፍሬ ያለው ነገር ማበርከት እንዳይችሉ ዕንቅፋት ሆኖባቸዋል ።" [30] በማለት ነው የስንፈት ኩታቸውን በማውለቅ ሊገፍፉላቸው በማሰብ ምክኒያት አብጅተውላቸዋል ።

በወቅቱ ብሩሕ አእምሯቸውን በመጠቀም በንቃት ለኢስላምና እና ለሙስሊሞች ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ድንቅ ሥራዎችን የሰሩ ጥቂቶች ነበሩ ። ሆኖም በነዚህ ጥቂቶች የልፋት ውጤት ላይ መሠረት ተደርጎ የሌሎቹ ስንፈት ተሸፋፍኖ የሚታለፍ ጉዳይ ባለመሆኑ ከላይ የጠቀስነው ሕግ እንደጸና ይኖራል ። አዎን የስንፈትን ኩታ የተላበሱ ትውልዶች የተቦካውን ከመጋገር ይልቅ መልሰው ያቦኩበታል እንጂ ለማህበረሰባቸው ጋግረው ዳቦ አድርገው በማብሰል አያቀርቡለትም ።

ሸይኹል ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ በሕይወት ዘመናቸው ለስኬት እንዲበቁ ካደረጓቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ በወቅቱ የተሞላ የመጽሐፍት ቤተ -መዘክሮች ከነኢንሳይክሎፔዲያቸው (ከያዙት ሁሉን አቀፍ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር) ተሰናድተው መገኘታቸው ምቹ አጋጣሚን ፈጥረውላቸዋል ። ሱንናዎች በዝርዝር ተቀምጠውም ነበር ። መዝሃቦች በመጽሐፎች ተጠናቅረው ዝግጁ ነበሩ ። ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ ያነበቧቸው መጽሐፍት ብዛት ስንት ሊደርሱ እንደሚችሉ ማንም ሊገምት አይችልም ። በየትኛው ሸይከ አካሄድ ተጽእኖ ሥር ወድቀው ወደ አካሄዱ እንደተዘነበሉም ለመግለጽ አይቻልም ።

ለጋስነታቸው

ማንኛውንም ጠያቂ ወይም ለማኝ በባዶ መልሰው አያውቁም ። በቻሉት ሁሉ የለመናቸውን ሰው ወይም የጠየቃቸውን ሰው ለግሰው ይሸኛሉ ። የሚሰጥ ነገር ቢያጡ እንኳን ልብሳቸውን አውልቀው ይለግሱ ነበር ። አልሐፊዝአልበዛር እንደዘገቡት ((*ቁርአን የሚያቀሩት ታላቁና ከቡር ሊቅ ሸይኽ አቡ ሙሐመድ ዐብዱሏህ ብኑ አሸ–ሸይኽ አሰ–ሷሊሕ አል–ሙቅሪእ አሕመድ ብኒ ሰዒድ « ከዕለታት አንድ ቀን ከሸይኽ ተቂዩዲን ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ዘንድ ተቀምጬ ሳለ አንድ ግለሠብ ወደኛ ዘንድ መጣ ። ይህ ግለሠብ ጥምጣም የሚያሰፈልገው ሰው መሆኑን ሸይኹ አሰተውለው ዓማኢማቸውን ከአናታቸው አውልቀው ለሁለት ከከፈሉት በኋላ ግለሠቡ ሳይጠይቃቸው ሰጡት » ብለው ነገረውኛል ።*))[31]

አልሐፊዝ በዛር ((*የምተማመንበት ግለሰብ እንደነገረኝ « ሸይኽ ተቂዩዲን ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ በአንድ ጠባብ መንገድ አየተጓዙ ሳሉ አንድ ድሃ ሰው ዱዓ አደረገላቸው ። ሸይኹም የዚህን ድሃ ችግር ተረዱ ። በወቅቱ የሚሰጡት ገንዘብ ግን አለነበራቸውም ። የለበሱትን ልብስ አውልቀው ሰጡት ። «በሚያወጣልህ ዋጋ ሸጠውና ለችግርህ አውለው ። » ካሉት በኋላ ልብሳቸውን የሰጡበት ምክኒያት በጥሬው* ሊሰጡት የሚችሉት ገንዘብ በእጃቸው ላይ ስለሌለ እንደሆነ ከይቅርታ ጋር ገለጹለት))